የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 37.
ADDIS ABABA 27th May, 2008

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፩/፪ሺህ ዓ.ም

የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፩፻፭

**CONTENTS**

**Proclamation No. 581/2008**

Water Resources Development Fund Establishment and Administration (Amendment) Proclamation Page 4105

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፩/፪ሺህ

### <u>የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፩/፪ሺህ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ማ ሻ ሻ ያ</u>**

የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፰/፲፱፻፺፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፯/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፯/ ተተክቷል፣

## PROCLAMATION NO. 581/2008.

### A PROCLAMATION TO AMEND THE WATER RESOURCES DEVELOPMENT FUND ESTABLISHMENT AND <u>ADMINISTRATION PROCLAMATION</u>

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Water Resources Development Fund Establishment and Its Administration Proclamation;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Water Resources Development Fund Establishment and Administration (Amendment) Proclamation No. 581/2008".

**2. <u>Amendment</u>**

The Water Resources Development Fund Establishment and Its Administration Proclamation No. 268/2002 is hereby amended as follows:

1/ Sub-Article (7) of Article 2 of the Proclamation is repealed and amended by the following new Sub-Article(7):



ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

«፯/ 'ተቋም' ማለት የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ድርጅት፣ እንዲሁም የመስኖ የህብረት ሥራ ማህበር ነው፤»

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፰/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፱/ ተጨምሯል፣

«፱/ 'ተዘዋዋሪ ፈንድ' ማለት ከተበዳሪዎች ተመላሽ የሚደረግና ጽሕፈት ቤቱ ለተበዳሪዎች መልሶ የሚያበድረው ገንዘብ ነው፤»

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተተክቷል፣

«፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ዕውን ለማድረግ ወጪን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሠረተ የረ ¡ ም ጊዜ ብድር ማበደር።»

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተተክቷል፣

«፫/አበዳሪዎችና ለጋሽ ድርጅቶች ወለድን በሚመለከት የሚያስቀምጡት ቅድመ ሁኔታ ከሌለ ቦርዱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚወስነው ጣሪያ ሳያልፍ በብድር ላይ የሚከፈለውን የወለድ መጠን ይወስናል።»

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተተክቷል፣

«፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከተደነገገው በተጨማሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ /፬/ መሠረት በቦርዱ የሚፀድቁ መመዘኛዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ። »

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፬/ እና /፭/ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፬/ እና /፭/ ተተክተዋል፣

«፬/ ቦርዱ በሚያፀድቀው የብድር አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት በየዓመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፭/ መሠረት የሰበሰበውን ገንዘብ ለተበዳሪዎች በብድር ይሰጣል። »

"7/ 'Institution' means urban water supply and sanitation service providers and irrigation cooperative association';

2/ The following new Sub-Article (9) is added under Article 2 of the Proclamation:

"9/ 'Revolving Fund' means the fund collected from borrowers and loaned to borrowers by the office".

3/ Sub-Article (3) of Article 4 of the Proclamation is repealed and amended by the following new Sub-Article (3):

"3/ To grant, for the realization of the objectives stated in Sub-Articles (1) and (2) of this Article, long term loans on the basis of the principle of cost recovery".

4/ Sub-Article (3) of Article 5 of the Proclamation is repealed and amended by the following new Sub-Article(3)

"3/ Unless there are certain preconditions laid down by creditors and donors, the Board shall determine the interest rate payable on loans and such rate shall not exceed the ceiling set by the Ministry of Finance and Economic Development,

5/ Sub-article (2) of Article 7 of the Proclamation is repealed and amended by the following new Sub-Article (2):

"2/ In addition to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the criterion approved by the Board pursuant to Article 14(4) of this Proclamation shall be applicable".

6/ Sub-Articles (4) and (5) of Article 11 of the Proclamation are repealed and amended by the following new Sub-Articles (4) and (5):

"4/ Grant loans out of the money collected pursuant to Sub-Article (5) of this Article upon evaluating the annually submitted requests on the basis of the criteria approved by the Board".

«፭/ ለፈንዱ መግባት የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኘውን ተሰብሳቢ ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ ይሰበስባል፣ በፈንዱ ሂሳብም ገቢ በማድረግ በተዘዋዋሪ ፈንድ ይዞ ለተመሳሳይ የብድር አገልግሎት ያውለዋል።»

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"5/ Make timely collection of repayment of loans and interests as well as all money to be collected from sources mentioned under Article 5 of this Proclamation and deposit the same in the account of the Fund as a revolving fund for similar purpose of lending service to borrowers".

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of May, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**